## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ፤አሜን ! ።

## "ለኢትዮጵያ እንደ አገር መቀጠል መልህቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን መታደግ ነው

"ለእኔ ለገብርኤል ብዙነህ ፥ቅድስት ሃይማኖታችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህደ ዕምነት ብቻ ሳትሆን፤ የአገር እና የህዝብ ቀስተዳመና ናት ብዬ አምናለሁ። ይህም ብቻ አይደለም፤ የቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ቅኔ የሚገለጠው በሰው እና በተፈጥሮ መካከል ሊኖር የሚገባውን የሰመረ ግንኙነት አንባቢ፤ ተርጓሚ፤ አማሳጣሪ በመሆን ብቻ ሳትሆን፤ በተጨማሪም አስማሚ፤ አግባቢ፤ ዳኛና ችሎትም ሚዛንም ናት ። ቅድስት የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ለተፋጥሮም፤ ለሰውም የምትሰጠው ፍቅር ሰማያዊ ጸጋዋ ነው የሚል ሙሉ ዕምነት አለኝ። ለእኔ ሃይማኖታችን ሰብዕአዊም፣ ተፈጥሯዊም ናት። ብሄራዊም፣ ዓለም- አቀፋዊም ናት። ስለሆነም እግዚአብሔር ለፈጠራቸው ፍጥረታት፤ ነፍሳት፤ የተፈጥሮ ጸጋዎች፤ ምድርና ሰማይ፤ ጋራው እና ሸንተረሩ፤ ወንዙና ወቅያኖሱ፤ ሃይቃትና ሸለቆው፤ አዝእርቱ እና እጽዋቱ፤ ነፋስና አየሩ፤ ሙቀት እና ቅዜቃዜው፤ ወቅታት እና ዘመናት፤ ማዕልትና ግርማ ለሊቱ ሁለ በተፈጠረላቸው ሥነ – ምግባር መሰረትንት በሰላም ውለው ያድሩ ዘንድ፤ ለእናት አገሬ ኢትዮጵያና ለዓለም ተግታ ትጸልያለች ። በትጋት ትጽማለች፤ ባልተቋረጠ ሁኔታ ትሰግዳለች፤ በተከታታይ ምህላ ትይዛለች፤ አቅዳም ሱባኤም ትቆጥራለች። አምላኳንም ተግታ፤ በጥንካሬና በብርታት ታመሰግናለች። ይህ ች ጥንታዊትየኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋሕድ ቤተ ክርስቲያን ይህንን በማድረጉዋ ዛሬ ላይ በዚህ ትዉልድ ዘመን በአራዊታዉያን እርመኞች ስትቃጠል ስትነድ አማኞችዋ ሲታረዱ ሲሳደዱ ቅጥሩዋ ሲፈርስ ከማየት የበለጠ ሞት የለም በቁም መሞት ፤ያሜል። አራዊታዉያን ራሳቸው ጠፍተዉ ለሰዉና ለአገር ጥፋት በዘግናኝነት ቤተ እምነታችንን ሲያጋዩ ታዳጊዎችን ሲያሳቅቁ የተዋህዶ ጠበቆች የት ናቸዉ ? የትነን? ክፉ ዘመን ! በለዉጥስም የሰረጉ አራዊታዉያን የሰዉን ጥንተ ጠላት የዲያብሎስን ተግባር በቤተክርስትያን ላይ ሲፈጽሙ ክብሯን በአደባባይ ሲያዋርዱ ፤አልሰማንም ይሆን ? አላየንም ይሆን እየኖርን ይሆን...! ።ክርስትያን በመሆኑ ብቻ ሰዉን ሰው አድኖ መአትን ሲያወርድበት ቆሞ መመልከት፤ ሲያቃጥለዉ ዝም ፥ በተለይም በከፋ ሁኔታ ቤተከስትያንዋን በሚያዋርድ እንዳለን በማያስቆጥር ድፍረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኝ ታዳጊና የወደፊቱ የቤተክርስትያንዋ መሪዎችና እምነትዋ አስቀጣዮች የመንበርዋ ተረካቢዎችና ሃብቶችዋ የሆኑት ታዳጊ ህፃናት ለትምህርት ወደ መማሪያ ክፍሎቻቸዉ ከመግባታቸዉ በፊት በር ላይ አንገታቸዉ እየተፈተሸ ማተብ ያሰሩ እንዳይገቡና እንዲመለሱ የመደረጉ እማኝ ሰቅጣጭ ተግባር በእዉነት ኢትዮጵያ ዉስጥ ሆነ ለማለት ክብዶ ያስለቅሳል።አዬ አዬ አገሬ አዬ ኢትዮጵያ እግዚአብሄር ያጽናሽ።አለቀስኩልሽ ! ።

ይህ አራዊታዊ አደና መቆሚያዉ የት ነዉ ? በነገር ሁሉ በተዋህዶ ልጆች ላይ፤ክርስትያን በመሆናቸዉ ብቻ ግፍ ሲፈጸም ዝም ማለት ከክህደት ይቆጠራል።ሰዉን ሰው ሲያቃጥለዉ ዝም ማለትና ቆሞ መመልከት በጥሞቲዎስ 5 ፡8 ላይ እንደተነገረ ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የከዳ ከማያምን ሰዉ ይልቅ የከፋ ነዉ ብሎ ቅዱስ ጳዉሎስ የተናገረዉን መሆን ነዉ።ክርስትና እምነታችን ከረጅሙ ታሪካችን ከኢትዮጵያዊ ባህላችን ዉጭና በላይ ህገ አራዊት ርቆ የሄደ በምንም ቋንቋ ቢገለጥ አንገት ከማስደፋት በላይ ነዉ።ከዚህ ቀደም በእነዚህ ህገ አራዊታዉያን በእምነቱ ሲታረድ ሲቃጠል ሲታነቅ ሲሰደድ ቤቱ ሲፈርስ ጎርፍ ላይ ሲተኛ ዝም ጭጭ አልን፤ አባት እንደሌላቸዉ ሆን ፤እየሰማን እያየን ቅዱስ ጳዉሎስ እንደተናገረ ቤተሰብነታችን ካድንና መዘባበቻ ሆን ፥እኮ ለምን ? ጸሎታችንስ ምኑ ላይ ነዉ ? ቅጥያጣ ዝምታችን እየነደደች ስባለች ቤተ ክርስትያናችንና እየተወጋ እየታረደ እየተገደለ እየተሰደደ ጎርፍ ላይ እየተኛ ባለዉ አማኝ ላይ ተቀባይነት የሌለዉና በሞራል የለሽነት በአዉሬነት ከገዳዮች አራዊታዉያን ጋር የሚያስመድብ አይሆንምን? የአለፉት የተዋህዶ አርበኞች አጽም አይፈርድብንምን ? ። ስለዚህ ዛሬ አሁን እንደ አንድ ሰዉ ከምትቃጠለዉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያናችንና እየታረደና እየተወጋ ከሚሞተዉ ከሚሰደደዉ አማኝህዝባችን ጋር በመቀላቀልና ዝምታችንን በመስበር የእርመኞች አራዊታዉያንን የጥፋት ተግባር ልንጋፈጠዉና ልናስቆመዉ ይገባል አሁን።ግፉ ያስገድደናል። በዚህም

ይህንንም እንድጽፍ ያሳሰበኝ፤ በኢትዮጵያዊነቴ፤ የታሪክ፤ የመንፈስ ፤ የሞራልና የስነምግባር ሃላፊነት ጭንቀት የነገሩ ክብደት፤ እጅግ ግዙፍ ዓይነት ሸክም ሆኖ ስለተሰማኝ ስለታዬንኝ እረፍትም ስለነሳኝ ሲሆን ፤ለዚህም አንኳር ጉዳይ ፤ በኦርቶዶክስ ጠል ምስለኔዎች የጠላት ሴራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን መቃጠል፤የልጆችዋ መታረድ፤መገደል ፤መወጋትና መሰደድ፤ታሪካዊ ንዋየ ቅዱሳትዋ መዘረፍና ቅጥሮችዋ በመፈራረስ አጥተናል በዘመኑ ትልቁ ድፍረትበቤተክርስትያን ላይ ተፈጽሞ ተፈትነናል።ጭራሽ የአማኝዋን አገራዊ ማንነታችን ማንኮታኮት፤ድካምን ሁሉ በመናድ ለማጥመድ በተሸረበዉ ሴራ

ሳንወሰድ አሁን ቀበቶአችን በማጥበቅ በአንድነት መቆምና ከፊታችን ያለዉን ተራራ በማለፍ ወደነበረዉ ኢትዮጵያዊ የእምነት ማንነታችን ለእዉነተኛ ፍትህና ነፃነት ከመገስገስ መቆም አንችልምና የምንፈተንበት ጊዜዉ ሆንዋልና መንጋቱ አይቀሬ ነዉና በተባበረ ግዝፈት ማለፍ አሁን በመሆኑ ለቤተክርስትያናችን መከበር ለአማኝዋ ሰላም በመሽቀዳደም፤የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንጉዳይ ከንብረት ከኑሮ የበለጠ ክብር የምንሰጠዉ ሃቅ ነዉና አራዊታዊያን በኢትዮጵያ ምድር የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን በማቃጠል ልጆችዋን በማረድና በማፈናቀል የማሳደድ የእሳት ኣቧራ ኣስነስቶኣልና ይህንን በተዋህዶ ጠል ምስለኔዎች የተቀነባበረብንን ሴራ በመቀራረብ በአፋጥኝ መፍትሄ መስጠት አለበት ብየ በማመን ፤ሌላ አለመረጋጋት ሊዘረጋ ስለሚችል ካለማስተዋል በጠላት የጥፋት ድግስ ኢላማ ሥር ቤተክርስትያንና ህዝባችን እንዳይወድቅ በመስጋት እጂግ አሳሳቢ የአካባቢ አደገኛ ቀዉስ፤ ጥፋት ዉስጥ እንገኛለንና ነዉ። በመሆኑም በዉጭና አገር ዉስጥ የምንገኝ ወገኖች ይህንን እብሪት ለማስቆም በአንድ ድምጽ መንቀሳቀስ ግድ ሆንዋል፤

ችግሩ በየጊዜው እየከፋ በጣም እየጎላ በመሄዱ ከወዲሁ ትኩረት ተሰጥቶት ለችግሩ መፍትሄ ቢሰጥ፤የየኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንህልዉና የተከታዮችዋ ሰላም ፤ለኢትዮጵያ እንደ አገር መቀጠል ጠቀሜታዉ የጎላ እንደሚሆን ና፤ቅዱስ ጳዉሎስ እንደተናገረ "በስለት ሰይፍ ላይ ብትቆም እራስህን ትጎዳለህ" እንዳለ በአገር ዉስጥ የሚያስተጋባዉን ጩህትና ስነ ልቦና ተመልክተን መፍትሄ ቢደረግ (ቢሰጠዉ) መልካም ሲሆን፤ አሁን ጠላት አራዊታዊያን በደገሰልን ከእርስት የመነቀል የህልዉናጥፋት፤ድግስና እዉነትን በጥቅም በቀየሩ፤ ቅጥረኛ ደላሎች፤ በማያስተዉሉ፤ በዉስጥ በሰረጉ የጥፋትአስፈጻሚ እጆች በያዙት ሸካራ ፤የባሩድና ቤተክርስትያንን የማቃጠል በሽታ መንገድ መቼ ም ቢሆን መስማማት ሊኖር እንደማይችል ከመቼውም ጊዜ በላይ ግልጽ እየሆነ እየመጣ ያለና ፤ኢትዮጵያዉያንን ያስደነገጠ ተግባር ተስተዉሎኣል። እናም በዚህ ዲያብሎሳዊ አካኼድ ወደ ሌላ የከፋ የጥላቻ፣ ታሪክ ምዕራፍ ከመሻገራችን በፊት የሴረኞችን የጥፋት መንገድ ለመዝጋት፤ በመታደግ አገርና ትዉልዱ ከገባበትና እየነጎደ ካለበት የቂም በቀል አዙሪት መታደግ የኢትዮጵያን ህልዉናዋን፤እድገቷን ለማየት ለሚያስብ ለማን ኛዉም ኢትዮጵያዊ የተሻለ መሆኑን በማሳሰብ ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን፤በታሪክ ለኢትዮጵያ አገሩዋ የለዉጥና እድገት ሂደት እንቅፋት ያልሆነች ፤ ሆናም ያልቆየች እንዲያዉም ለአገር ሰላምና አንድነት ልጆችዋን እየገበረች እራስዋም እየነደደች አስተዋጽኦ ስታደርግ የነበረች ያለችና ወደፊትም የሚትኖር ታላቅ ኢትዮጵያዊ አለም አቀፋዊ ክርስቶሳዊ የእምነት ቤት ነችና አሁን በቀን ጎደሎነት ለገጠሙት የህልዉና ፈተናዎች መፍትሄ ባናደርግ እኛን በዚህ ትዉልድ የምንገኝዉን ሁሉ መብላቱ አይቀርምና እራሳችንን በራሳችን እኛነታችንን እንታደገዉ ። ወገናችንን ሲጨርሱት ሲያስጨርሱት ሲያጫርሱት መጨረሻ በሌለው የእርም በደል ያልነኩትና ያልዳሰሱት መሞከሪያ የለም ፤አራዊታዉያን ሁሉንም በኛ ላይ ፈትሸዋል ሞክረዋል ። በታሪካችን ያልሰማነው ግፍና በደል እየደረሰብን ገፍተን ያለመሄድ ቅጥያጣ ዝምታ፥ እኛም ተመቻቸንላቸው እነርሱም በማቃጠል ተዝናኑብን ።አንዳንዴ የሌለብን እርግማን ያለብን ይመስለኛል ። እናም ያልተበደርነውን ለአራዊታዉያን ሌባ እርመኛ የቀን ጅቦች በመታረድ እየከፈልን እንገኛለን ትግሉ መሯል ከምጽአት ቀን በፊት መዉጪያው ዉርደትን መመከት ነዉ ለታሪክ እርሾ ሆኖ እንዲያገለግል ።ስለዚህ" ለከፉዎች፡ሰላም፡የላቸውም፡ይላል፡እግዚአብሔር፡በኢሳ፡48/22 ይላልና ምነልባትም አራዊታዉያንእርመኞችና ወኪሎቻቸው የሚያደርጉት ስትራቴጂ መረን የለቀቀና ምን ታደርጉናላችሁ ዓይነት በዕብሪት የተሞላ ፈተና ሊመጣ ይችላልና የላላዉን በመወጠር የተወጠረዉን በማላላት ረገድ ወቅትና ሁኔታን በማጥናት ለአፍታ ሳንዘናጋ ቤተክርስትያንን በህብረት ከአራዊታዉያን "እርመኞች ነቅተን በመጠበቅ የምናጣው ሀሰተኛ ወዳጅን ብቻ ነው" እናም ፥ የአገር ጉዳይ በአንድ መሪ ፍላጎት፣ ድካምና ጥረት ብቻውን የሚጠናቀቅ ሥራ አይደለምና፤በመንግሥት ደረጃ በተቋቋሙ ተቋማትና ባለሙያዎች እንዲሁም በሕዝቡ ድጋፍና ተሳትፎ የሚጠናቀቅ ጉዳይ ነውና፤ ለኢትዮጵያ ዳግም ላለማልቀስ በመተባበር የሌሎች ነፍስ መታደግ ና ኢትዮጵያ አገራችንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስቤተክርስትያንንና አማኞችዋን ከአራዊታዉያን እርመኞች መዋረድን ለማስቆም መውደቅ መነሳቱ ምን ጊዜም አለና፣ በመከራ ና በፈተናም በመፅናት ፤ ወደ ሰላም እንደምንሻገር ጥርጥር የለኝም። ነገር ግን ይህን ማድረግ ተስኖን ከተሸነፍን፣የተሸነፍነው በእርመ ኞች ዱለታ ሳይሆን በእኛ በፅናት አለመተባበር መሆኑን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ልብ ልንለዉ ይገባል።መጽሐፍ በዜና መዋዕል ቀዳማዊ "እስራኤልም የሚገባውን ያደርግ ዘንድ ዘመኑን የሚያውቁ ጥበበኞች ሰዎች የይሳኮር ልጆች አለቆች ሁለት መቶ ነበሩ።" እንዲል ዘመንን ስለ መመርመር እና መዋጀት የእያንዳንዳችን ኃላፊነትና ግዴታ ለመሆኑ ማሳሰቢያ የሚያስፈልገው አይመስለኝም። በተጨማሪም የሀገር ደህንነትና እና የሕዝብን የሰላም፣ የዲሞክራሲ፣ የፍትህና የነፃነት ጥያቄ ጉዳይ በተመልከተ እንደ ተስፋ ቢስ ወቅትን እየጠበቅን ያዙኝ ልቀቁኝ የሚባል ዓይነት ሳይሆን ያለመታከትና መሰላቸት ሰላማዊ በሆነ መንገድ

እርምጃዎቻችን ሊያስከፍሉን የሚችሉ መሥዋዕቶች ለመክፈል በመወሰን የሚደረግ ጉዞ ነው። አሁንም በአገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቦችዋ ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋና እየከረፋ እየሄደ ያለውን ዘግናኝና እና አሳፋሪ ፖለቲካዊ የአየር ጸባይ መመርመር ግድ ነውና ፥ዛሬ በአገራችን እየሆነ ያለው እጣፈንታው አንድ በሆነ ሕዝብ መካከል የተዘራው አቤልና ቃኤልን የሚያስንቅ የጥላቻ ፖለቲካ ነው። የኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሔ ሊመነጭ የሚችለው ፈረንጆች እንደሚሉት ወደ drawing boardዱ ተመልሰን ባለፉት 28 የመከራ አመታት ውስጥ ኢትዮጵያን የማያውቋትና ኢትዮጵያን ይዘው የወረዱበትን ቁልቁለት በእውቀት መመርመር ከጀመርን ብቻ ነው። ጸረ ኢትዮጵያዉያን በደረቱት የፈጠራ ዝባዝንኬ እየተጓዝን የተለየ ውጤት መጠበቅ ትርፉ መድረሻችን አሁን ያጋመስነው እንደ አገር የመኖር እጣችን ለጊዜውም ቢሆን ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት አለያም የሚያቆምበት ደረጃ መድረስ ብቻ ነው። ይህንን የሚጠራጠር ካለ እስካዚያው ሳይቃጠል ከቀረ ብርታቱን ይስጠው እንጅ በአራዊታዉያን ወደ ማቃጠያ ሜዳው እየዘለቅን ስለሆነ ሲደርስበት ያየዋል። « ብሔር፣ ብሔረሰቦች» የሚባሉት ሁሉ ኢትዮጵያ በምትባል ዛፍ ስር የበቀሉ ሳሮች መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው። ተወደደም ተጠላም ሁላችንም ዛፍ ስር የበቀልን ትንንሽ ቁጥቋጦዎች ነንና ዛፉ ሲወድቅ የምንጠፋው ሁላችንም አብረን ነው። የተቆረጠ ካርታ አንጠልጥሎ ሲዞር የሚውለው ሁሉ ግን ቁጥቋጦ መሆኑንና ይህን ማሰብ አይፈልግምና ብርቱ ጉዳይ ኢትዮጵያ አገሬን ይጠብቃታል። የኢህ አ ዴግ መንግስትም ቢሆን ይህንን የቤተክርስትያንን ቃጠሎና ዉድመት የአማኝችዋ ሞትና ስደት በግልጥ ሊያወግዝና በማስቆም " ለኢትዮጵያ እንደ አገር መቀጠል መልህቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን መታደግ መሆኑን" ለሽማምንቶቹ እስከታች የወረደ ሴሚናር ሊያዘጋጅ ይገባዋል።ካሁን በሁዋላ የአልሰማሁም የአላየሁም ዧዋዥዌ ጊዜዉ ያለፈበት ፈሊጥና አገርና ህዝብን ፤ ኢህ አ ዴግን ብዙ ዋጋ ያስከፍላል።

የ3ተኛዉ መንግስተ ኢህ አ ዴ ግ የለዉጥ ሃይል መሪ ዶ/ር አቢይን የመደመር ጉዞ ስደግፍ መነሻየ አሳሳቢ ጉዳየ የቤተክርስትያንኔ ጉዳይ ነበር ፤በቤተክርስትያን በሁለት ሲኖዶስ መከፈል ችግር የእንባችን ተጋ ሪዎች ጓዶኞቼና የፍቅር ጣሪያ አባቶቼ ጋር በመሆን በሰቀቀን ለ13 (አስራሶስት) አመታት እልህ አስጨራሽ የቤተክርስትያን አባቶችን የማስታረቅ ጉዞ በራሳችን ተነሳሺነትና በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ የተሰበሰብን ኮሚቴ አቁዋቁመን ጥረታችንን ቀጥለን ። ለአቶ መለስ ፤ለአቡነ ጳውሎስ ፤ለመቶ አለቃ ግርማ ፤ለአቶ ሀይለማሪያም ፤ለአቦይ ጽሃየ ወዘተ.. የሁለንም በር አንኩዋኩአን ፥ወ/ሮ አዜብም አልቀሩን ፥ሁለንም ተማፅኖ አሰማን ደብዳቤም ጽ ፈን ፥ ለቤተክርስትያን እርቅ ሁሉን ም ምንጭ ተጠቀምን -እግዚአብሔር ይርዳችሁ ከሚለዉ የወ/ሮ አዘብ መፅናኛ ቃል በስተቀር ፤ለቤተክርስትያናችን እርቅ ሁለም ምንጮች ደረቆች ነበሩ። የሚረዳን አጥተን ኤሎሄ ኤሎሄ አልን ፤የሞተ የተረሳ ነበር ።እርቅ ማለታችን እንደ ተስቦ በሽታ ተቆጥሮ ብን ። እንዳዉም እርቅ የሚለሉጣቶች ይቆረጣሉ ብለውን ነበር። ነበርም ቀላል ከሆነ። ያንን ዘመን ሳስብ ፤ስንቶች ይህችን በመደመር የተገኘች የቤተክርስትያን እርቅ ቀን ሳያዩ ግን ተመኝተዋት አፈር እንደተጨአናቸው ሳስብ ሰዉ መሆን ያስጠላል ፥ሁሌም አለቅሳለሁ በተለይም አቡነ ዜናማርቆስ ከአሜሪካ፤ አቡነ አብሳዲ ከኢየሩሳለም፤ አቡነ መርሃ ክርስቶስ ከትግራይ፤ አቡነ ሕርያቆስ ከኢየሩሳሆም ሀገረስብከቶችና ሌሎችንም ኢትዮጵያዊያንን ወገኖቻችን አባቶችና ምዕመናንን ሳስብ። እርቅ ብለን ረቂቅ የውስጥ ጉዳቶች ተጎዳን ። ውስጣችን በእጅጉ ተጎሳቁሎሎ። ውስጣችን ዕንባ የከተመበት፤ ውስጣችን በሃዘን ብዛት የከሰለ፣ የጠወለገም ነበር ። ተስፋችን ጥግ አጥቶ በተሰደድንበት በፈለስንበት እየ መከርንበት ስንኖር ፤ባለፉት 26 አመታት የቤተክርስትያን መከፋፈል እርቅ ፍለጋ ስንከራተተት ሰሚ በጠፋበት፤ስለመኖርዋም ግድ በሌላቸዉና አለመኖርዋን በሚያልሙ ፤።ጠላት ዲዛይን ባደረገዉ የጥፋት አረም መንገድ አሠራር "ኢትዮጵያዊነት" ተቀብሮ ኢትዮጵያዊነትን ተጻይፎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን በመለያየት በማበላላት ገድሎ የኢትዮጵያ መሪ የኾኑ ፤በጎቹን እየጠላ የበጎች እረኛ ባየንባት ፤አገሩን በአግባቡ በማይጠራ ትውልድ ምድር በከፉዎች ፋንታ ባላሰብነዉና ባልጠብቅነው መንገድ በዶ/ር አብይ የሚመርዉ የመደመር ለዉጥ ሃይል (ቡድን) ከነማህበረ ጲላጦስና ከማህበረ ደራጎን ህወሃታዊ ኢህዴግ የቁም እስረኝነት አንድ ለአምስት ከመጠርነፍ ራሱን አላቆ ኢትዮጵያዊነትን እየሰበከ ለቤተክርስትያን እርቅ ኦርቶዶክስ አገር ነች እያለ፤ነገን ለማቆዬት ቀኗ ሳታልፍ በጊዜዉ ተጠቅመንበት ወደ ታሪካችን፤ ወደ ባህላችን ለመመለስ የስራዉ መጀመሪያ ያደረገዉና የፈቀደዉ የስኬታችን የብልህነት ሰልፍ የእርቅ ማዕድ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕድ ቤተ ክርስትያን ፤የቤተክርስትያን ኣባቶች በሲኖድሳዊ ሰላምና እርቅ ፤የሰላምና -የእርቅ ቀን፤ ለእርቁ ከይሁንታ ጀምሮ ማናቸዉንም አስፈላጊ ጉዳዮች በማሟላት በቅርበት ሰዉ በመመደብ ታሪክ የሚዘከረዉ ስራ ስርቶአል። በመከፋፈል ሲቃ የመከፋት ዘመን ሰቆቃ የቆይታ ጊዜ እንዲያከትም በመደመር ፍቅር ማሽነፍ ሆነ ያን የቤተክርስትያን የእርቅ ረሃብ ቁጭ ብለን በጉባዔው ተሰይመን ትንሳዔውን አዬን፤ አዬሁት። ተላቀስን … አነባን ። ቅጽበቱ እጅግ ይደንቅ ነበር። ትዕይንት ነበር የሚመስለው። እጅግ ይመስጣል።

እጅግም ያጽናናል። እጅግም ይፈውሳል ተደራዳሪ አባቶች የሰሩት አኩሪ ሥራ የዘመናት ሃዘኔን በፍቅር እንባ አጥቦታል። መችም ቢሆን አልረሳቸዉም። እኔ በቤተክርስትያኔ እርቅ ትፍስህት ተሰምቶኛል። እኔ ሰናይ ተሰምቶኛል ። እኔ ፍሰሀ ተሰምቶኛል። እኔ ህይወት ተሰምቶኛ። እኔ መኖር ተሰምቶኛል።" ሰው ያስባል እግዚአብሔር ደግሞ ይፈጽማል" ተፈጸመ ። የድጋፌ መስመር መነሸያየ ይህ ነበር ! ። በመሆኑም ምንም እንኳዋን በአንድ ጀምበር ማግስት ሁሉም ይስተካከላል የሚል ሃሳብ ባይኖረኝም ከቶ ፤ የኢትዮጵያንኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን አገርነት የተረዳዉ የ 3 ተኛዉ መንግስተ ኢህ አ ዴ ግ የለዉጥ ሃይል እንደ መንግስት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በአራዊታዉያን ስትነድ ምእምናኖችዋ ሲጠቁ ሲታረዱ የመረጃዉ መረብ በጁ እንዳለዉ መጠን ቢቻል ጥቃት ከመድረሱ በፊት አለመታደጉ በዚህ ተያያዡ ጉዳይ ዙሪያ፤ተዋህዶ ሃይማኖታችን አጠቃላይ የሁሉም መለኪያችን የማትናወጥ መሰረት ናትና በዚች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖታችን መመዘኛ ስንመዝነዉ ቢያንስ ሰብአዊነትን አለመታደጉ የህገ አራዊታዉያን መንገድ እንደተጠረገላቸዉ ያስቆጥራል። ይህም ያስፈራል።ይህ የቤተክርስትያን መቃጠልና የአማኞችዋ መታረድ ሞትና ስደት ኢትዮጵያን ለማፍረስ አገርን መጀመሪያ ወደ ጫካነት የመለወጥ ሳጥናኤላዊ መንገድ ነዉና ጉዳዩ ከምንም በላይ ግድ ሊለዉ ይገባል። ይህ በታሪክ የሚያስጠይቅ አራዊታዊ አስቆሮታዊ ባህሪ ኢትዮጵያና ህዝቡዋን የሚበላ የጥፋት መርዝ በተግባር ሲዉል ዝምታዉ ፋታ ወደመስጠት ያዘነበለ አስመስሎታል። ምን አልባትም በእቅፉ ያሉ የሚመለከታቸዉ ሃላፊዎች በመደመር በጎነት ላይእንደ ሌሳዉ ኢትዮጵያዊ ብኩርናን የሸጠ የተፈጽመ ክህደት መስሎ ተሰምቶናል።በመሆኑም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ስለ ሰዉ ክብርና ልዕልና የሚገልፅትን ቅዱሳት መጽሃፍት ማቃጠል ቅጥር ማፍረስ ቤተ መቅደስ ማቃጠልንዋየ ቅዱሳትን መዝረፍ ካህናትንና ምእመናን ልጆችዋን ማዋረድና መግደል ሊያስቆም ይገባል።

ከፉ ቀን እስኪ ያልፍ ድረስ ያለፋልና ትልቁ ጥያቄዬ የሳምሶን ጠላቶች ዓይኑን ብርሃን አጥፍተው ሲያበቁ ዝፈንልን በማለት በአደባባይ እንደተሳለቁበት ሁሉ የዚህ ምስኪን የኢትዮጵያ ሕዝብ መጨረሻ ዕጣ ፈንታስ ምን ይሆን? ከፍ ካለው በላይ ከፍታን የያዘ ወገኖቹን እስራኤላውያን ከግብፃውያን የባርነት ህይወት ነጻ ያወጣና ፈርዖንን በባህር የቀጣ ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነቱ ካሃሊነቱ ሳይዘነጋ፤በጣም በጣም ጥቂትም ቢሆኑ በጣት የሚቆጠሩ ስለእዉነት በመቆም ከመጀመሪያዉ በደል ይብቃ እያሉ ጊዜዉን የሚዋጁ የሚጮሁ አባቶች እንዳሉን ሁሉ ፤ካርታው ለጠፋባቸውና ተዘልለው ለተቀመጡ፤ ማለቴም ፥ ሰብአ ሰገልንም ይመራቸው የነበረ ኮከብ የጠፋባቸው ከተማ የገቡ ዕለት መሆኑን ሳስተውል በኢትዮጵያ ምድር ለሚገኙ በእግዚአብሔር ሥም ኑሮአቸውን ላደላደሉ የኃይማኖት መሪዎች በሚታየዉ አይን ያወጣ መፈናቀል እንግልት ስደት ግፍና መከራና እስራት ዝምታ ጭጭታ ለመጪው ትውልድ እያስተላለፉችሁት ያለው መልዕክት ቢኖር ግን ኃይማኖት ስለ እግዚአብሔር እንደማይናገር መሆኑን ልብ ልትሉ ይገባችኋል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ " ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል" ሲል ከደቀመዛሙርቱ መካከል ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ "አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ?" ሲል እንደመለሰለት እናንተን (የኃይማኖት መሪዎች) ትኩር ብሎ ያየስ ማንን ይከተል ይሆን እግዚአብሔርን? ወይንስ ? ይከብዳል! ዛሬም እናንተ የኃይማኖት መሪዎች ምን አገኛችሁ? እንደ በልዓም አስመጣችሁ ልበል ወይስ በእስራኤል ዘንድ ይነግሥ ዘንድ ንቄዋለሁ ተብሎ እንደተነገረለት እንደ ሳዖል ለሥልጣናችሁ ስትሉ ወከባውን በመፍራት ነው ዝምታን የመረጣችሁ? የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሞቀ ጎጆው ተፈናቅሎና ተሰዶ አገርና ሰው እንደሌለው መጠልያ አጥቶ በየጎዳናው ሲንከራተት የማንም መሳለቅያ ሲሆን - እናንተ ትተኛላችሁን፥ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር።" እንዳለው በዚህ የዝምታ የአመጻ ሥራ ተሰማርታችሁየአባትነትአንደበታችሁ ከሚሸበብ ኑራችሁ ከምታልፉ ጠቢቡ (መጸሐፈ መክብብ ምዕራፍ ፬ ከቁጥር ፩ እስከ ፫) እንዳለው ገና ያልተወለደው ከፀሐይም በታች የሚደረገውን ግፍ ያላዬ ይሻላል።" እንዳለ ባልተወለዳችሁ ይሻላችሁ ነበርን? ግን ንቁ ኧረተወልዳችሁ ለመንጋዉ ተሹማቹሃል።¬ ሕዝብ በህገ አራዊት የፖለቲካ ደላሎች ቃል የተነሳ በዋይታና በለቅሶ እረፍቱን ሲያጣ፤ ሰላሙ ርቆበት በኣራዊታውያን ሲወገር፤ ረዳት ፍለጋ ሲቅበዘበዝ ፤ክቡሩ የሰው ልጅ መንገድ ላይ ሲወድቅ፤- በምንጣፋችሁ ላይ ተደላድላችሁ ትቀመጣላችሁን? ፥ አማኝ ፥ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በረሀብ አለንጋ እየተገረፈ ሲሳደድ እናንተ መቸ ነዉ ድምፃችሁን የምታሰሙ? አራዊታዉያን እርመኞች የኢትዮጵያ ህዝብ ለቅሶና ወይታ እንደ መሰንቆ ድምጽ ራሳቸዉን ሲያዝናኑበት፣ እንባው የወይን ጠጅ የመጣጣት ያህል ሲያረካቸዉ፤ ለመሆኑ ስለ ተዋህዶ አማኝ ህዝብ መከራና ስለ ምድሪትዋ ጉስቁልና ግድ የማይላችሁ የማይቆረቁራችሁና ደንታ ቢሶች የሆናችሁ ምን አይነት የአዚም ፍልስፍና ነው? ወይንስ ዛሬም የምደባ ሃሳብ አባዜ ዉስጥ እንደሰመጣችሁ ነዉ? እስቲ ድምፃችሁን እንስማ

*ዝምታችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ዳግም በሞት መንገድ እንዲሰቃይና እንዲመሰቃቀል፤ይጎሳቆል ዘንድ ይሁንታችሁን መስጠታችሁ ክልሆነ በስተቀር  ከቶ ምን ይባላል።ወይንስ እንደ ባሳን ላሞች ሆነናል እጅግ የደለብን ሃሳብ አልባ።፤ የባሳን ላሞች በመጽሐፍ ቅዱስ በአሞጽ መጽሐፍ ላይ የሥነ-ምግባርም እና የሞራል ውድቀት የገጠማቸውን የከሰሩ የኃይማኖት መሪዎች ተክቶ በምጸት ቋንቋ ተጽፎ የምናገኘው። ነገሥታት የሀገር መሪዎች  ባለጊዜዎችበግፍ ህዝባቸውን ያለ አግባብ ሲጨቁኑና ሲያጎሳቁሉ በወቅቱ የነበሩ “ የኃይማኖት መሪዎች” መጽሐፍ ገልጠው አፋቸውን ከፈተው ከህዝባቸው ጎን በመቆም አመጸኞችን በመቃወምና በማውገዝ የተገፉትን ደግሞ በማጽናናት ፈንታ ስለ ሚመሩት ምእመን ግድ የማይላቸውና ደንታ ቢሶች መሆናቸውን ሳስብ ጊዜዉን የሚዋጁ እዉነተኛ አባቶችን ፍለጋ በብዙ ሽህ ማይል ልቤ በየገዳማቱ ሲቃትት ይነጋል ።እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ በሚደርሰው ኢ-ፍትሐዊ (ፍትህ አልባ) ድርጊቶችና በህዝቦች ላይ በሚደርሰው ግፍና በደል ግድ ይለዋል። ምዕመን ተስፋው  ፈጣሪው፤ ሃይማኖቱ፤ መላዕክታት፤ ሰማዕታት፤ ቅዱሳን ደናግላን፤ ሀገሩ፤ ብቻም ሳይሆን የመንፈስ አባቶቹም እራኞቹም ናቸው።እባካችሁ፤*

*ለዚህ ነው ነቢዩ አሞጽ እግዚአብሔር ግድ ስለሚለው ነገር ግድ ስለማይላቸው  የኃይማኖት መሪዎች መጨረሻ ሲናገር ዓሶች በመንጠቆ እንደሚጠመዱ እንዲሁ በረከት ይዞ ይመጣል ብለው በሚያስቡበትን የጌታ ቀን የቅጣትና የጥፋት ሆነባቸው ሲል የሚናገረውና። እግዚአብሔር ቸር መሃሪ አምላክ ነውና እውነትን እውነት ውሸትን ደግሞ ውሸት ትሉ ዘንድ ኃይልና ብርታት ሁሉን ከሚችል ከእግዚአብሔር አምላክ ትቀበሉና ቤተ-ክርስቲያን የእግዚአብሔር አፍና ጆሮ መሆንዋንና“ ለኢትዮጵያ እንደ አገር መቀጠል መልህቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን መታደግ መሆኑን ትገልጡት ና ”እኛነታችንን እንታደገው” ዘንድ የልጅነት ጥሪዬን አቀርባለሁ።*

*ባጠቃላይ ይህ የአራዊታዊ እርመኞች ቡድን ማንኛዉንም  መንገድ ተጠቅሞ የስልጣኔ መሪ የጽድቅ መንገድ ብርሃን የሆነች ጥንታዊና ታሪካዊትዋን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በማንደድ አማኝዋን በማረድ ዘግናኝ ግፎችን በመፈጸም  መሰረትዋን በማጥፋት ሁሉንም ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያን የመግደል ፕሮጀክት ሆኖ ስለተሰማኝና አምላኬ በተአምሩ ከማህበረ ደራጎን ማህጸን የለዉጥ ሰዎችን አስነስቶ በግፍ የወደቀዉን የኢትዮጵያ ህዝብና ኢትዮጵያዊነትን ሊያነሳ ነዉ በሚል የመደመር ተስፋ ተሸርሽሮ ባልተጠበቀ አኩዋኩሃን መከራችን በበዛበት በዚህ አስጨናቂ ጊዜ ቤተክርስትያንን ከፉኛ ስለጎዳት፤የቤተክርስትያን ጥፋት ዘገር ነቅናቂዎች በፈርሃ  እግዚአብሔር ባልተገታ ፍጻም ኢ-ቤተክርስትያናዊ ፤ኢ-ኢትዮጵያዊ  ኢ-ሰብአዊ ጉዞ ደግመን እንድናስብ ተገደናልና ይህንን የአራዊታዉያንን የሞት ደወል ልንጋፈጠዉና ልናስቆመዉ ይገባል።ለዚህ ደግሞ የታሪክ የትዉልድ የቤተክርስትያንና የቀደሙ የዋኖቻችን አባቶቻችን የተዉት አደራ ሃላፊነቱ ዛሬ የእኛ ነዉ ።በህያዉ የእምነት ጉዞዋና ታሪክዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በእምነትዋ ለሰዉ ልጅ ነጻነት  ለአፍሪቃና ለሌሎች የአለም አገሮች ምሳሌና እናት ሆና የኖረችበትን መንገድ ሁሉ ዛሬም ልጆችዋ ለመድገም በዓለም አደባባይ በአንድ ድምጽ እንንሳ እንሽቀዳደም።”እኛ እንነሳ እግዚአብሄር አምላክ ያከናዉንልናል”።ነገ ሰላም ይሆናል።*

*“ ለኢትዮጵያ እንደ አገር መቀጠል መልህቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን ን መታደግ የሰላም ምልክት መሆን ነዉ” !!!*

*“እግዚአብሔር  በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል። ሰው ግን አያስተውለውም።“(መጻህፈ እዮብ ምዕራፍ ፴፫ ቁጥር ፲፬)*
*"ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር" እግዚአብሔር አገራችን ኢትዮጵያን ይባርክ ።*

*ገብርኤል ብዙነህ (ሰሜን አሜሪካ)* 08/16/2019